# የዱር እንስሳት የታክሲ ደርሚ ንግድ መመሪያ ቁጥር 846/2014

**የዱር እንስሳት የታክሲ ደርሚ ንግድ**

**መመሪያ ቁጥር 846/2014**

የዱር እንስሳት ሃብት ባልተቀናጀና አግባብነት በሌለው አጠቃቀም ምክንያት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተመናመነና ለአደጋ ተጋላጭነቱ እየጨመረ በመምጣቱ፤

በዱር እንስሳትና በዱር እንስሳት ውጤት ላይ የሚደረገው የንግድ የዱር እንስሳቱን አደጋ ላይ የማይጥልና ህጋዊ በሆነ መንገድ እንዲከናወን ማድረጉ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የዱር እንስሳት በፍጆታዊ የአጠቃቀም ስልት አማካይነት ከዱር እንስሳት ሃብት የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በማጎልበት ለሀገሪቱ ልማት የሚያበረክተውን አስተዋጽዖ ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በዱር እንስሳት የታክሲደርሚ ንግድ ሥራ ላይ የሚስተዋሉ የአሠራር ክፍተቶችን በማስወገድ ወጥነት፣ ተጠያቂነት፣ ግልጽነትና ፍትሃዊነት የሰፈነበት የአሠራር ሥርዓት እንዲፈጠር ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀፅ 31 የተሠጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች በአግባቡ ለመወጣት ይህንን መመሪያ አወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የዱር እንስሳት የታክሲ ደርሚ ንግድ መመሪያ ቁጥር 846/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1. **"ታክሲደርሚ"** ማለት የሞቱ ወይም በህጋዊ መንገድ የታደኑ ዱር እንስሳትን ውጤቶች በመጠቀም እንስሳቱን አስመስሎ መሥራትን ወይም የእንስሳቱን ውጤት አዘጋጅቶ ማቅረብን የሚያጠቃልል ሥራ ነው፡፡
2. **"ፍጆታዊ አጠቃቀም"** ማለት የዱር እንስሳትን ከመኖሪያ ቦታው በመውሰድ ወይም በስፖርታዊ አደን፣ በራንች ወይም ዕርባታ በማሳደግ ለውጤታቸው (ሥጋ፣ ቆዳ፣ ላባ፣ቀንድ፣ጥርስ) ሲባል በመግደል የመጠቀም ስልት ነው፡፡
3. **"ፈቃድ"** ማለት ለታክሲደርሚ ሥራ ከባለሥልጣኑ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡
4. **"ሚኒስቴር"** ማለት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ነው፤
5. **"ባለስልጣን"** ማለት የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ነው፡፡
6. **"ሰው"** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

3. ***<u>የመመሪያው ዓላማ</u>***

1. የዱር እንስሳት ሀብታችንን የአጠቃቀም ስልቶች ስብጥርን በማሳደግ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የበኩላቸውን እንዲያበረክቱ ማድረግ፤
2. የዱር እንስሳት ወጤቶች ንግድ ሥራን ጥራት ባለው መልኩ እንዲስፋፉ ማበረታታት፤
3. ለዱር እንስሳት ታክሲ ደርሚ ሥራና ንግድ ህጋዊና ወጥነት ያለውን የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት፤
4. በታክሲ ደርሚ ሥራ ምክንያት የዱር እንስሳት ላይ የሚደርሰውን ተጽዕኖ መቀነስ፤

4. **<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ መመሪያ የታክሲ ደርሚ ሥራ በሚያከናውን ሰው ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የዱር እንስሳት የታክሲ ደርሚ ንግድ ሥራ

### 5. መሠረት

1. ማንኛውም ሰው በዱር እንስሳት ታክሲደርሚ ሥራ ለመሰማራት ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡
2. ለሌሎች ፍጆታዊ የአጠቃቀም ዓይነቶች ያልተፈቀዱ የዱር እንስሳትን ለታክሲደርሚ ሥራ ለማዋል ከባለሥልጣኑ ልዩ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት የተዘጋጁ ጎፍላዎችና የታክሲደርሚ ውጤቶች ለትምህርት፣ ለሳይንሳዊ ምርምርና ለሙዝየም አገልግሎት ብቻ መዋል አለበት፡፡

### 6. የዱር እንስሳት ታክሲ ደርሚ ሥራ መስፈርቶች

ማንኛውም ለዱር እንስሳት ታክሲደርሚ ሥራ ፈቃድ የሚጠይቅ ሰው የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፤

1. ከንግድ ሚኒስቴር የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፤
2. የታክሲ ደርሚ ሙያ ሥልጠና ማስረጃ ወይም አግባነት ያለው የታክሲ ደርሚ ሥራ ሙያ ልምድ ወይም የታክሲ ደርሚ ባለሙያ የቅጥር ውል ማስረጃ፣
3. ለታክሲ ደርሚ ሥራ የሚያገለግሉ አስፈላጊ መሣሪያዎች፣
4. ለሥራው ተስማሚ የሆኑ አስፈላጊ ክፍሎችና ግቢ ያለው ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ፣
5. ዓመታዊ የፈቃድ ክፍያ መክፈል የሚችል ወይም ለመክፈል ውል የገባ፣

### 7. የታክሲደርሚ ባለሙያዎች መስፈርት

1. የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ያጠናቀቀ፣
2. የታክሲ ደርሚ ትምህርት በታወቀ ተቋም ከ3 ወር በላይ የተከታተለና የማለፊያ ውጤት ያገኘ ወይም በታክሲ ደርሚ ሥራ ከ4 ዓመት በላይ የሥራ ልምድ ያለው ስለመሆኑ ከታክሲ ደርሚ ድርጅቶች ወይም ከተመሳሳይ ተቋም ማስረጃ የሚያቀርብ፣

3. ስለ ዱር እንስሳት ዓይነትና የመኖሪያ አካባቢያቸው ዕውቀት እንዳለው የጽሁፍና የቃል ፈተና ማለፍ፣

## 8. ስለጥያቄ አቀራረብ

1. ለታክሲደርሚ ሥራ ፈቃድ የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው የጽሁፍ ማመልከቻና አስፈላጊ መረጃዎችን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡
2. ባለሥልጣኑ የቀረበውን ማመልከቻ ገምግሞ በአንድ ወር ውስጥ ምላሽ ይሰጣል፡፡
3. የቀረበው ጥያቄ ያልተሟላ ሆኖ ከተገኘ በ15 ቀን ውስጥ መረጃውን አሟልቶ እንዲያቀርብ ይመለስለታል፡፡
4. ፈቃድ ጠያቂው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ መረጃውን አሟልቶ ካላቀረበ ጥያቄው ይሰረዛል፡፡

## 9. ፈቃድ የተሰጠው ሰው ግዴታ

1. ለዱር እንስሳት ታክሲ ደርሚ ሥራ የሚውሉትን እንስሳት ወይም ውጤቶች ምንጭ፣ የማሳደኛ ወይም የማጥመጃ ዘዴ፣ የሚሰጠውን የዱር እንስሳት ታክሲ ደርሚ ሥራ አገልግሎት ደረጃና ጥራቱን ገላጭ ጽሁፎችንና ማስረጃዎች በግልጽ የማሳየት ወይም የመለጠፍ፣
2. የተሟላ የሥራ ሪከርድና ሠነዶች አደራጅቶ የመያዝ፣
3. የዱር እንስሳት የታክሲ ደርሚ ሥራ አገልግሎት ደረጃና ጥራቱን የመግለጽና ለምርመራ አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ ለሚመለከተው አካል ግልጽ የማድረግ፣
4. ባለፈቃዱ የተሟላ የንግድ ሥራ ስያሜ፣ አድራሻ (ክፍለ ከተማ ፣ወረዳ፣ የቤት ቁጥር)፣ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ስልክ፣ ፋክስና ኢሜል ለተገልጋዮች በግልጽ በሚታይ ቦታ የማስቀመጥ ወይም የመለጠፍ ፡፡
5. የዱር እንስሳት ታክሲ ደርሚ ሥራ ከማከናወኑ በፊት ለታክሲደርሚ ሥራ ጥቅም ላይ የሚውለው የዱር እንስሳ ውጤት በህጋዊ መንገድ የተገኘ መሆኑን የማረጋገጥ፣
6. ፈቃዱን ለተሰጠው ዓላማና ተግባር የማዋልና የሙያውን ሥነ-ምግባር የማክበር፣
7. የታክሲደርሚ ሥራውን የብቃት ማረጋገጫና የሥራ ፈቃድ በሚያቀርብ ባለሙያ ብቻ የማከናወን፤
8. ከሥራው ጋር በተያያዘ ፈቃድ ከተሰጣቸው አካላት ጋር ህጋዊ ውል የመግባት፤

9. ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የታክሲደርሚ ሥራ አገልግሎት የመስጠት፣
10. ስለዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የወጡትን ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች የማክበር፣

## 10. <u>ስለክትትልና ቁጥጥር</u>

1. ባለሥልጣኑ የታክሲደርሚ ሥራና ውጤቶችን በተመለከተ ዓመታዊ ግምገማና ቆጠራ ያከናውናል፣
2. ባለሥልጣኑ ለታክሲደርሚ ባለሙያዎች የአቅም ግምባታ ሥልጠና ሊሰጥ ይችላል፡፡
3. ባለሥልጣኑ የታክሲደርሚ ሥራ በሚከናወኑባቸው ቦታዎች ላይ ቁጥጥር ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 11. <u>ግዴታን ባለማክበር ስለሚወሰድ እርምጃ</u>

ማንኛውም የታክሲደርሚ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ሰው፡-

1. ከተፈቀደለት ዱር እንስሳ ውጤት ውጪ ሲጠቀም ከተገኘ የሥራ ፈቃዱ ለ2 ዓመት እንዲታገድ ይደረጋል፡፡
2. የተሰጠውን ፈቃድ ለሌላ ላልተፈቀደለት ሕገወጥ ተግባር ሲያውል፣ የዱር እንስሳት ውጤት በሕገወጥ መንገድ ሲነግድና ከሁለት ጊዜ በላይ ጥፋቶችን ሲፈጽም ከተገኘ የተሰጠው ፈቃድ ይሰረዛል፡፡
3. ለታክሲደርሚ ሥራ የተሰጠውን ፈቃድ በሚሰጠው የጊዜ ገደብ ሳያድስ ቢቀር ፈቃዱ ለስድስት ወር ይታገዳል፡፡
4. ስለዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የወጡትን ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ተላልፎ ሲገኝ እንደሁኔታው ታይቶ ፈቃዱ ሊሰረዝ ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

12. **የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ ውስጥ የተጠቀሱትን የአሠራር ሥርዓቶች ለማስፈፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

13. **ቅጣት**

ሕጋዊ ፈቃድ ሳይዝ የታክሲደርሚ ሥራ ሲያከናውን የተገኘ ማንኛውም ሰው አግባብነት ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

14. **ቅሬታዎችን ስለማስተናገድ**

1. በፈቃድ አሠጣጥም ሆነ መሠረዝ ምክንያት ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ቅሬታውን በ30 ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. በባለሥልጣኑ መልስ ያልተስማማ ቅሬታ አቅራቢ አቤቱታውን ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ይችላል፡፡

15. **ስለተሻሩ ሕጎች**

ከዚህ መመሪያ በፊት የነበረው የዱር እንስሳት ታክሲ ደርሚ መመሪያ ተሽሮ በዚህ መመሪያ ተተክቷል፡፡

16. **መመሪያውን ስለማሻሻል**

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

17. **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከሰኔ 1 ቀን 2007 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡